የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፳
አዲስ አበባ ታህሳስ ፳፮ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

19th Year No. 20
ADDIS ABABA 4th January 2013


<u>ማውጫ</u>


አዋጅ ቁጥር ፯፻፸፰/፪ሺ፭ ዓ.ም

፬ኛውን የመንገድ ዘርፍ ልማት ለሚደግፈው የትራንስፖርት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም ዓቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ .............ገጽ ፮ሺ፯፻፴


<u>CONTENTS</u>


Proclamation No. 778/2012

International Development Association Financing Agreement for the Transport Sector Project in Support of the 4th Road Sector Development Program Ratification Proclamation ....... Page 6730


### አዋጅ ቁጥር ፯፻፸፰/፪ሺ፭

### <u>በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም ዓቀፍ የልማት ማኅበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ</u>

፬ኛውን የመንገድ ዘርፍ ልማት ለሚደግፈው የትራንስፖርት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ፪፻፸፫ ሚሊዮን ፭፻ሺ ኤስ.ዲ.አር (ሁለት መቶ ሰባ ሦስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ ስፔሻል ድሮዊንግ ራይትስ) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም ዓቀፍ ልማት ማህበር መካከል እ.አ.አ ኦክቶበር ፲፰ ቀን ፪ሺ፲፪ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ታኅሣሥ ፲፰ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### PROCLAMATION No. 778/2012.

### <u>A PROCLAMATION TO RATIFY THE FINANCING AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION</u>

WHEREAS, a Financing Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a credit amount of 273,500,000 SDR (two hundred seventy three million five hundred thousand Special Drawing Rights) for financing Transport Sector Project in Support of the 4th Road Sector Development Program was signed in Addis Ababa on the 18th day of October, 2012;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Financing Agreement at its session held on the 27th day of December, 2012;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

| | |
|---|---|
| ያንዱ ዋጋ<br>Unit Price | 2.30 |

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "፬ኛውን የመንገድ ዘርፍ ልማት ለሚደግፈው የትራንስፖርት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም ዓቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፯፻፸፰/፪ሺ፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. የስምምነቱ መፅደቅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም ዓቀፍ የልማት ማህበር መካከል እ.አ.አ. ኦክቶበር ፲፰ ቀን ፪ሺ፲፪ በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 5155-ET በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

**፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፪፻፸፫ ሚሊዮን ፭፻ሺ. ኤስ.ዲ.አር ( ሁለት መቶ ሰባ ሦስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ ስፔሻል ድሮዊንግ ራይትስ) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**፬. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ታህሳስ ፳፮ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Financing Agreement for the Transport Sector Project in Support of the 4th Road Sector Development Program Ratification Proclamation No. 778/2012".

**2. Ratification of the Agreement**

The Financing Agreement Credit No. 5155-ET signed in Addis Ababa on the 18th day of October, 2012 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association is hereby ratified.

**3. Power of the Ministry of Finance and Economic Development**

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the credit amount of 273,500,000 SDR (two hundred seventy three million five hundred thousand Special Drawing Rights) in accordance with the terms and conditions set forth in the Financing Agreement.

**4. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 4th day of January, 2013.**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት